በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አፈጻጸም ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2011 ዓ/ም

አዲስ አበባ

መውጫ

ድርሞ /Excutive Summery/ 1

ክፍል አንድ 4

መግቢያ 4

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አመሰራረት 4

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ራዕይ 5

ራዕይ 5

በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 995/2009 ኢ.ም መሰረት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተግባርና ኃላፊነት 5

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል 6

የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ የፋይናንስ ምንጭ 7

የኦዲቱ አላማ 7

ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ 7

ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች እና የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች 7

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች 7

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች 8

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ 8

የኦዲቱ ወሰን 8

የኦዲቱ ዘዴ 8

የአሰራር ስርአት መግለጫ 10

.... 10

ክፍል ሁለት 11

ግኝቶች 11

ባንኩ የተሟላ እና ትክክለኛ የሂሳብ መዛግብት መያዙን በተመለከተ 11

ባንኩ ስለፈንዱ ገንዘብ አጠቃቀም ሪፖርት ማቅረቡን በተመለከተ 13

ባንኩ የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች ማስተላለፉን በተመለከተ 16

ባንኩ የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በሌሉባቸው አካባቢዎች ቅርንጫፍ ባንኮች ተክተው እንዲሰሩ ማድረጉን በተመለከተ 18

ባንኩ የፈንዱን ሂሳብ እንዲመረመር ማድረጉን በተመለከተ 20

ክፍል ሦስት 24

የኦዲቱ መደምደሚያ (Audit Conclusion) 24
ክፍል አራት 27
የኦዲቱ ማሻሻያ ሀሳብ (Recommendation) 27
አባሪዎች i
አባሪ 1-የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ድርጅታዊ መዋቅር /C Level/ i
አባሪ 2- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የመመዘኛ መስፈርት ii

ድርሞ /Excutive Summery/

ኦዲቱ የተከናወነው የመንግሥት መ/ቤቶችን የክዋኔ ኦዲት ለማድረግ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሲሆን የክዋኔ ኦዲቱ አላማ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አፈጻጸም በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ ስለመሆኑ ለመገምገም ሲሆን በዚሁ መሰረት በኦዲቱ የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው፣

1. ለፈንዱ ከተመደበው በጀት ብር 10,000,000,000 ውስጥ ከ9 ቢሊየን ብር ማለትም ከ90 % በላይ ከመንግስት ወጪ ሆኖ ለክልሎች /ለተጠቃሚዎች/ እንዲተላለፍ የተደረገ ቢሆንም የፈንዱን ሂሣብ በሚመለከት ኦዲቱ እስከ ተከናወነበት ጊዜ የተሟላና ትክክለኛ የሆነ የሂሳብ መዛግብት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክም ሆነ በሌላ አካል እንዲያዝ አለመደረጉ፡፡
2. ባንኩ በአዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀጽ 11/2 መሠረት ስለፈንዱ ገንዘብ አጠቃቀም ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የሚቀርብለትን ሪፖርት በማጠቃለል በየስድስት ወሩ፣ እንዲሁም በአንቀጽ 15/2 መሠረት የተመረመረ የፈንዱን ሂሣብ ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በየዓመቱ ሂሳቡ በተመረመረ በአንድ ወር ውስጥ ለገንዘብ ሚኒስቴር አላቀረበም፡፡ ለፈንዱ ከተመደበው 10 ቢሊየን በጀት ከ90 % በላይ ወጪ ሆኖ ሳለ፤ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማትም ለተጠቃሚዎች ያሰራጩት የፈንዱን ገንዘብ ኦዲት አለማድረጋቸው እና ኦዲት እንዲያስደርጉም ያልተደረገ መሆኑ፡፡
3. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀፅ 9/1 እና 2 /በየክልሎቹ ወጣቶች ቁጥር/ መሠረት በ2009 እና 2010 በጀት አመት የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይንንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች እንዲተላለፍ ማድረግ ሲገባው፤ነገር ግን ከ9.1 ቢሊዮን ብር በላይ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ የተደረገው በአዋጁ ከተገለፀ ውጭ ውክልና በሰጣቸው የዘጠኙ ክልሎች እና የሁለቱ ከተማ መስተዳድር ፋይናንስ ቢሮዎች በኩል ከመሆኑም ባሻገር፤ የገንዘብ ሚኒስቴር ባንኩ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ገንዘቡ ወደ ተጠቃሚዎች

የሚያስተላልፉበት ደንብና ሁኔታዎች ባለወጣበት እና በአዋጁ ስልጣን ባልተሰጣቸው በየክልሉ የሚገኙ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በተዘጋጁ ወጥነት በሌላቸው ደንቦች እና ሁኔታዎች መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰቡ ሰነዶችና ለሚመለከታቸው ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ከተደረጉ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት መቻሉ፡፡

4. የአዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀጽ 11/1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በሌሉባቸው አካባቢዎች ቅርንጫፍ ባንኮች የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማትን ተክተው እንዲሰሩ አላደረገም፡፡ እንዲሁም ባንኩ በአዋጁ ከተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ውጭ ለዘጠኙ ክልሎች እና ለሁለቱ ከተማ መስተዳድር የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች ውክልና ሲሰጥ በውክልና ውሉ ላይ እንዲካተት አላደረገም፤ በመሆኑም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በሌሉባቸው በኢትዮጵያ ገጠር ወረዳዎች ውስጥ የሚኖሩ ወጣቶች የፈንዱ ተጠቃሚ መሆናቸው /አለመሆናቸው/የማይታወቅ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት በቀረቡ የሰነድ ማስረጃዎች እና ለሚመለከታቸው ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ከተደረጉ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት መቻሉ፡፡
5. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የ2009 ዓ/ም እና የ2010 ዓ/ም የፈንዱን ሂሣብ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ እንዲመረመር አላደረገም፤ በአዋጅ ከተሰጠውን ስልጣን ውጭ ውክልና ከሰጣቸው ውስጥ በናሙና ባየናቸው የትግራይ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ የሀረሪ ክልሎች እንዲሁም የአዲስ አበባ እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ቢሮዎች የፈንዱን ሂሳብ በዋናው ኦዲተር ወይም እነሱ በሰየሙት ኦዲተር በየዓመቱ እንዲመረመር ያልተደረገ መሆኑ፡፡

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማስተዳደር በአዋጅ 995/2009 ዓ/ም በክፍል ሁለት አንቀጽ ሰባት ኃላፊነት ቢሰጠውም፤ ባንኩ የመወከል እና በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣን አሳልፎ ለሌሎች አካላት የመስጠት ስልጣን ሳይኖረው ስራውን ሳይጀምረው ለዘጠኙ ክልሎች እና ለሁለቱ ከተማ መስተዳድር የፋይናንስ ቢሮዎች በውክልና ስልጣኑን የሰጣቸው መሆኑን በቀን 13/09/2010ዓ/ም የባንኩ ፕሬዚደንት በተገኙበት እንዲሁም በቀን 25/11/10 ዓ/ም የሚመለከታቸው

ኃላፊዎች በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ከገለጹት እና በቀን 01/10/2009 ዓ/ም በደብዳቤ ቀጥር ማኢ.-30/19/12 ከተጻፈ የውክልና የሰነድ ማስረጃ ለመረዳት መቻሉ፡፡

ክፍል አንድ

መግቢያ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አመሰራረት

6. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ባለቤትነቱ የመንግሰት ሆኖ ዋና መ/ቤቱን አዲስ አበባ በማድረግ የፋይናንስ አገልግሎት ይሰጣል፡፡ ባንኩ የተቋቋመው በ1942 ሲሆን ስያሜው የኢትዮጵያ መንግስት ባንክ " State bank Of Ethiopia" ይባል ነበር፡፡ በወቅቱ ቁጠባና የውጭ ሀገር ገንዘቦች /Saving and new currency/ ያስተዋወቀ ሲሆን፤ በአገሪቱ የተለያዩ ቦታዎች እና በሱዳንና በጅቡቲ ያሉትን ጨምሮ 21 ቅርንጫፎች ነበሩት፡፡
7. ባንኩ በ1963 አሁን ያለውን "የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ " ስያሜ ተሰጠው፤ በተጨማሪ ብቸኛ የማዕከላዊ ባንክ ሚና የሚጫወት /Role Of Central Bank/ እና የንግድ ባንክ አገልግሎት የሚሰጥ ነበር፡፡
8. ላለፉት 75 አመታት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአገሪቷ ትልቅ የፋይናንስ አገልግሎት ከመስጠቱም በተጨማሪ በፋይናንስ ዕድገት ትልቅ ሚና ተጫውቷል፡፡
9. በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ባለው መረጃ መሰረት፤ እስከ ሰኔ 30/2016 የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከጠቅላላው በባንክ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት /Banking Sector/ ከሚንቀሳቀሰው ተቀማጭ ውስጥ 66.1%ይይዛል፣ በባንክ ኢንዳስትሪው ከቀረቡ ብድሮችና ክፍያዎች ደግሞ52.6% ድርሻ አለው፣ በሀገሪቷ ካሉት የባንክ ቅርንጫፎች የ36.3 -- ድርሻ አለው፣ እንዲሁም በአገር አቀፍ ደረጃ ቅርንጫፍ ባንኮችን በመክፈት ቀዳሚ ነው፡፡
10. በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሁሉም የአገሪቷ አካባቢዎች በሚያስብል ሁኔታ ከ1230 ቅርንጫፎች በላይ፣ እና ከ33,000 በላይ ሰራተኞች ያስተዳድራል፡፡ /ምንጭ፡- 75th Commercial Bank Of Ethiopia Profile/
11. የልማት ግቦቻችን ስኬት በሀገራችን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ የወጣቶችን ቀጥተኛ ተሳትፎ የሚጠይቅ በመሆኑ፤ የወጣቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት

ለማረጋገጥ በገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች ተደራጅተው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቻቸውን እንዲያቃልሉ የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ በማስፈለጉ፤ ወጣቶች ያላቸውን ዕምቅ የማምረት አቅም ተጠቅመው በሀገሪቱ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ቀጥተኛ ተሳታፊ መሆን እንዲችሉ የሚያስፈልገውን የገንዘብ ድጋፍ ለማቅረብ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድን ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት አዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ/ምታወጇል፡፡

12. በአዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ/ም የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም በወጣው አዋጅ መሰረት የገንዘብ ሚኒስቴር፣ የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በቅደም ተከተል ፈንዱን ለማስተግበር መመሪያና ደንቦች የማውጣት፣ በፈንዱ ዙሪያ ስልጣን ያላቸው አካላት የማስተባበርና የመደገፍ እንዲሁም ፈንዱን የማስተዳደር ስልጣን የተሰጣቸው ቢሆንም በአዋጁ የተሰጧቸው ተግባርና ኃላፊነቶች ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ክፍተቶች ስላሉ እና የክዋኔ ኦዲቱን ማከናወን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በሦስቱ የመንግስት መ/ቤቶች የኦዲት ስራው ተከናወኗል፡፡
13. የኦዲት ሪፖርቱ በገንዘብ ሚኒስቴር፣ በሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር እና በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተናጠል የሚሰራ ሲሆን፤ ቀጥሎ የቀረበው የኦዲት ሪፖርት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ላይ የተሰራ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ራዕይ

ራዕይ

14. በ2025 እ.ኤ.አ በአለም ታዋቂ ከሆኑ ንግድ ባንኮች ተርታ ማሰለፍ ነው፡፡

በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 995/2009 አ.ም መሰረት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተግባርና ኃላፊነት

15. ቀጥለው የተዘረዘሩት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተግባርና ኃላፊነቶች ናቸው፡-

- ባንኩ በፌደራል መንግስት ስም ፈንዱን ያስተዳድራል፡፡
- በዚህ አዋጅ አንቀፅ 9/1 እና 2 መሠረት የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይንንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች ያስተላልፋል፤

- የዚህ አዋጅ አንቀጽ 11/1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በሌሉባቸው አካባቢዎች ቅርንጫፍ ባንኮች የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማትን ተክተው እንዲሰሩ ያደርጋል፤
- በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11/2 መሠረት ስለፈንዱ ገንዘብ አጠቃቀም ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የሚቀርብለትን ሪፖርት በማጠቃለል በየስድስት ወሩ፣ እንዲሁም በአዋጅ አንቀጽ 15/2 መሠረት የተመረመረ የፈንዱን ሂሣብ ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በየዓመቱ ሂሳቡ በተመረመረ በአንድ ወር ውስጥ ለገንዘብ ሚኒስቴር ያቀርባል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል

16. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሁሉም የአገሪቷ አካባቢዎች በሚያስብል ሁኔታ ከ1,230 ቅርንጫፎች በላይ እንዲሁም ከ33,000 በላይ ሰራተኞች አሉት፡፡ የባንኩ መዋቅር በስዕላዊ መግለጫ በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡

የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ የፋይናንስ ምንጭ

17.የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ብር 10 ቢሊዮን ሲሆን የፋይናንስ ምንጭ ከመንግስት በጀት ነው፤ ዝርዝሩ በሰንጠረዡ ተቀምጠዋል፡፡

የኦዲቱ አላማ

18.በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አፈጻጸም በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ ስለመሆኑ ለመገምገም ሲሆን በስራው ወቅት የተከሰቱ የአሰራር ችግሮች ካሉ መንስኤያቸውን በመለየት ችግሮችን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችል የማሻሻያ ሃሳቦችን በማቅረብ ተጠያቂነትን ለማስፈን ነው፡፡

ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ

19.ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ "የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አፈጻጸም ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን መገምገም" የሚል ነው፡፡

ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች እና የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች

20.ከላይ በተለየው የኦዲት አካባቢ ሥር አንድ ዋና የትኩረት አቅጣጫ እና ሦስት ንዑስ የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ ተለይተዋል፡፡ እነሱም ፡-

- ባንኩ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል መመሪያ ስለመኖሩና ተግባራዊ ስለማድረጉ መገምገም፡፡
- ባንኩ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል መዋቅር፣ የሰው ኃይልና የመረጃ ልውውጥ ስርአት ያለው ስለመሆኑ መገምገም፡፡
- ባንኩ በአዋጅ የተሰጡትን ዝርዝር ተግባራት ብቃት ባለው፣ በተቀላጠፈና ውጤታማ በሆነ መልኩ ስለመተግበሩ መገምገም፡፡

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች

21.በኦዲቱ አንድ ዋና እና ሦስት ንዑስ የትኩረት አቅጣጫዎች የተመረጡ ሲሆን እነዚህንም የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን ሚያስችሉ 5 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶችን (Evaluative criteria) ተለይቷል፡፡ በተዘጋጁት የትኩረት አቅጣጫዎችን እና የመመዘኛ መስፈርቶች ላይም የባንኩ ኃላፊዎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት ቀርቦላቸው ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ኦዲት መመዘኛ መስፈርት በአባሪ 2 ተያይዟል፡፡

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

የኦዲቱ ወሰን

22.በአጠቃላይ ኦዲቱ የተከናወነው በገንዘብ ሚኒስቴር፣ በሴቶች፣ ህጻናት እና ወጣቶች ሚኒስቴር እንዲሁም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሲሆን ኦዲቱ የሸፈነው ጊዜ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ በአዋጅ ከተቋቋመበት ከመጋቢት 2009 ዓ/ም እስከ 2010 ዓ/ም ያለውን የሥራ አፈጻጸም ነው፡፡ በትግራይ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሀረሪ ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባና ድሬደዋ ከተማ መስተዳድሮች የሚገኙ የፋይናንስ ቢሮዎች፣ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ቢሮዎች እና የተወሰኑ ብድር ወስደው ወደ ስራ የገቡ ኢንተርፕራይዞች በአካል በመገኘት ቃለ መጠይቅ በማቅረብ ነው፤ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት በያንዳንዳቸው መ/ቤቶች በተናጠል ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን፤ ይህ ሪፖርት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአዋጁ በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መሰረት ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው፡፡

የኦዲቱ ዘዴ

23.የኦዲቱ ዘዴ የሚያካትተው የኦዲት አካባቢውን የሚመለከቱ ሰነዶችን በመከለስ ከጉዳዩ ጋር የሚመለከታቸውን ተቋማት እና ባለድርሻ አካላት የስራ ሃላፊዎች ቃለ መጠይቅ በማድረግ እና በአስፈላጊ ቦታዎች በአካል በመገኘት መረጃ በመሰብሰብ የተከናወነ ነው፤፤በዚህ መሰረት የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ እና አግባብነት ባለው መልኩ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በመከለስ /በመተንተን፤ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለዘጠኙ ክልሎችና ለሁለቱ ከተማ መስተዳድሮች የፋይናንስ

ቢሮዎች በአዋጅ የተሰጠውን ፈንዱን የማስተዳደር ስልጣን በውክልና ያስተላለፈባቸው ሰነዶች እና ገንዘብ ሚኒስቴር ይህንን የውክልና ሰነድ ክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች እንዲተገብሩት መመሪያ ያስተላለፈበት ሰነድ በመከለስ፣ የሰነድ ማስረጃዎች በመሰብሰብ እና ምልከታ በማድረግ፣ የወጣቶች እና ስፖርት ሚኒስቴር ዕቅድና ዕቅድ ክንውን፣ የማኔጅመንት ቃለ ጉባኤዎች፣ ከከተማ መስተደዳድሮች እና ከገንዘብ ሚኒስቴር እና የወጣቶች የልማትና የውጤት ፓኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ የፌዴራል የክልል መንግስትና እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ያካተተ ሀገራዊ ስትሪንግ ኮሚቴ ሪፖርት በፌዴራል ተቋማት በክልልና በከተማ አስተዳደር ውይይት መድረክ ላይ በተነሱ ዋና ዋና ነጥቦች፤ በገንዘብ ሚኒስቴር የፈንዱን መመሪያዎች፣ ደንቦች እና ሁኔታዎች በተመለከተ ከህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በ11/11/2010 ለኦዲቱ የቀረበ ሰነድ፣ ከብሄራዊ ፕላን ኮሚሽን የሥነ ሕዝብና ስታትስቲክስ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የዘጡኑ ክልሎችና የሁለቱ ከተማ መስተዳድሮች ከ18-34 ዓመት ዕድሜ ክልል ያሉ የወጣቶች ብዛት የሚያሳይ ሰነድ፣ በገንዘብ ሚኒስቴር ለዘጡኙ ክልሎችና ለሁለቱ ከተማ መስተዳድሮች የተደረገው የፈንዱ የገንዘብ መጠን ክፍፍል የሚያሳይ ሰነድ፣ እንዲሁም ለሦስቱም ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የሚመለከታቸው ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የቀረበላቸውን ቃለ መጠይቅና አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በመሰብሰብ እና በመተንተን ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

የአሰራር ስርአት መግለጫ

24.የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ የአሰራር ስርአት መግለጫ የተዘጋጀው በኦዲቱ ሲሆን በስዕላዊ መግለጫ ይህን ይመስላል፡፡



ክፍል ሁለት

ግኝቶች

ባንኩ የተሟላ እና ትክክለኛ የሂሳብ መዛግብት መያዙን በተመለከተ

25. ባንኩ በየኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ/ም የባንኩ ተግባርና ኃላፊነት አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የፈንዱን ሂሣብ በሚመለከት የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ሊይዝ ይገባል፡፡
26. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከሚመለከታቸው የባንኩ የስራ ሃላፊዎች ጋር ባካሄዳቸው ቃለመጠይቆች እና የዶክመንት ክለሳዎች መሰረት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ሂሣብን በሚመለከት የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት እንዳልያዘ እና በአዋጅ የተሰጠውን ሃላፊነት እንዳልተወጣ በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
27. ከዚህ በተጨማሪ ባንኩ በአዋጁ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት በቀን 01/10/2009 ዓ/ም በደብዳቤ ቀጥር ማኢ-30/19/12 ለዘጠኙ ክልሎች እና ለሁለቱ ከተማ መስተዳድር የፋ/ኢ/ል/ ቢሮዎች በውክልና ሲሰጥ በውክልና ውሉ ላይ የሂሳብ መዛግብት መያዝ እንዳለባቸው እንዲካተት አለመደረጉ እንደ አንድ ክፍተት እንደሚወስደው እና የተሟላ የፈንዱን የሂሳብ መዛግብት የመያዝ ሀላፊነት ያለው አካል አለ ማለት እንደማይቻል በቀን 25/11/2010 ዓ/ም የሚመለከታቸው የባንኩ ኃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ላቀረበላቸው ቃለመጠይቅ ገልጸዋል፡፡
28. እንዲሁም በናሙና የታዩ የክልል እና የከተማ መስተዳድር ፋይናንስ ቢሮዎች ከገንዘብ ሚኒስቴር የተላከላቸውን የፈንዱ ገንዘብ ለማይክሮ ፋይናንሶች ስለማስረከባቸው እና ማይክሮ ፋይናንሶች ተጨማሪ ገንዘብ ለመጠየቅ ቀድመው የወሰዱትን ብር ስለማሰራጨታቸው ከሚገልጽ ማስረጃ ውጪ የተሟላ የፈንዱን

የሂሳብ መዛግብት አለመያዛቸው በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅና ካቀረቡት ሰነድ ለመረዳት ተችሏል፡፡

29. ስለጉዳዩ የባንኩ የበላይ ኃላፊዎች ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ፤ ባንኩ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለክልሎች በወከለበት ሰነድ መሰረት የባንኩ ግዴታ ውክልና የማስተላለፍ በመሆኑ፤ የፈንዱን ገንዘብ ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የሚተላለፍባቸውን ደንቦች እና ሁኔታዎች ለክልሉ ፋይናንስ ቢሮ የማሳውቅ ስራ የሚኒስቴሩ ግዴታዎች ዉስጥ የሚገኝ በመሆኑ በውክልናው አንቀፅ 3 ተ.ቁ 2 መመልከት እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡

30. በተጨማሪ ባለድርሻ አካላት ባንኩ ባዘጋጀው የተዘዋዋሪ ፈንድ ማስተዳደሪያ ረቂቅ መመሪያ ያላቸውን ቅሬታ ተከትሎ የገንዘብ ሚኒስቴር ከወቅቱ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚንስቴር እና የተለያዩ ከፍተኛ የመንግስት አካላት ጋር በተደረገ ልዩ ስብሰባ በጉዳዩ ላይ በጥልቀት ከተወያዩ በኋላ ባንኩ በአዋጅ ከተሰጠው ፈንዱን የማስተዳደር ተግባር እንዲያይ በጠቅላይ ሚንስትሩ በተቋቋመ ኮሚቴ ለስራው ቅልጥፍና ሲባል ባንኩ በአዋጅ ከተሰጠው ስልጣን እንዲወጣ የተደረገ መሆኑ የባንኩ የበላይ ኃላፊዎች በኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ገልጸዋል፡፡

31. የባንኩ የበላይ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ፡-

- አንደኛ በኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫው ላይ አስተያየት እንዲሰጥበት የቀረበው ጉዳይ ባንኩ የፈንዱን ሂሣብ በሚመለከት የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ስለመያዙና አለመያዙ ባንኩ ምላሽ እንዲሰጥበት የተጠየቀ ሲሆን የተሰጠው ምላሽ ባንኩ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለክልሎች በወከለበት ሰነድ መሰረት የባንኩ ግዴታ ውክልና የማስተላለፍ በመሆኑ የሚል ሲሆን ሊመለስ የሚገባው ጉዳይ፤ በአዋጁ ለባንኩ የተሰጠውን የፈንዱን ሂሣብ በሚመለከት የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት የመያዝ ሃላፊነቱን እራሱ እየፈፀመው ይገኛል ወይስ ይሄን ሀላፊነቱን ለክልሎች አሳልፎ ስለመስጠቱ መሆን ሲገባው የተሰጠው መልስ ግን ከጥያቄው ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌለው የፈንዱን ገንዘብ ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የሚተላለፍባቸውን ደንቦች እና ሁኔታዎች በተመለከተ የሚል በመሆኑ፤

- እንዲሁም አዋጁ በአዋጅ እስካልተሻረ፣ድረስ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት በውክልና ወይም በሌላ መንገድ ለሌላ ሦስተኛ ወገን የመስጠት ስልጣን የሌለው ከመሆኑም በተጨማሪ የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጅ ቁጥር 995/09 ክፍል ሦስት አንቀጽ 16 ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች በሚለው ክፍል ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በአዋጁ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት እንደማይኖረው በግልጽ ያስቀመጠ በመሆኑ፤ በመግባቢያው ሰነድ ደብዳቤ ቁጥር ማኢ-30/19/12 በተሰጠው ውክልና የክልል ፋይናንስ ቢሮዎች ባንኩን ወክለው የሂሳብ መዛግብት መያዝ እንዳለባቸው በአንቀጽ 4 በክልል ፋይናንስ ቢሮ ግዴታዎች እንዲካተት ያልተደረገ መሆኑ እንዲሁም ባንኩ የፈንዱ የሂሳብ መዛግብት ያልያዘ በመሆኑ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታው መግለጫ እና በኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ በባንኩ የበላይ ሃላፊወች የተሰጠው መልስ በኦዲቱ ተቀባይነት የለውም፡፡

32.ባንኩ የፈንዱን ሂሣብ በሚመለከት የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት አለመያዙ ወይም ሃላፊነቱን ለክልል የፋናንስ ቢሮወች ሲያስተላልፍ እነዚህ አካላት እንዲይዙ አለማድረጉ ለፈንዱ የተመደበው በጀት 10 ቢሊየን ብር በአግባቡ ስራ ላይ ስለመወዋሉ ወይም ስላለመዋሉ በትክክለኛ ማስረጃ ለማረጋገጥ ካለማስቻሉም በላይ የፈንዱን ሂሳብ በአግባቡ ለመቆጣጠር እና የሚመለከታቸው መንግስታዊ አካላት በተጨባጭ ማስረጃ ላይ ተመስርተው ውሳኔዎችን ለማስተላለፍ እንዳይችሉ ሊያደርግ እና የመንግስትና የሕዝብ ሀብት የሚቆጣጠር ተቋም ገንዘቡ በትክክል ለታለመለት አላማ ስለመዋሉ ለማረጋገጥ የሚደረገውን ሂደት ውስብስብና አዳጋች እንዲሆን በማድረግ ስለ አፈጻጸሙ ግልጽ ድምዳሜ ላይ እንዳይደርስ ሊያደርግና የፈንዱን አጠቃቀም አስመልክቶ ተጠያቂነትንና ግልፅነትን (Accountability and Transparency) ለማስፈን የሚደረገውን ጥረት ውጤታማ እንዳይሆን ያደርጋል፡፡

ባንኩ ስለፈንዱ ገንዘብ አጠቃቀም ሪፖርት ማቅረቡን በተመለከተ

33.ባንኩ በአዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀጽ 11/2 መሠረት ስለፈንዱ ገንዘብ አጠቃቀም ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የሚቀርብለትን ሪፖርት በማጠቃለል በየስድስት ወሩ፣ እንዲሁም በአንቀጽ 15/2 መሠረት የተመረመረ የፈንዱን ሂሣብ

ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በየዓመቱ ሂሳቡ በተመረመረ በአንድ ወር ውስጥ ለገንዘብ ሚኒስቴር ሊያቀርብ ይገባል፡፡

34. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከሚመለከታቸው የባንኩ የስራ ሃላፊዎች ጋር ባካሄዳቸው ቃለመጠይቆች እና የዶክመንት ክለሳዎች መሰረት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀጽ 11/2 መሠረት ስለፈንዱ ገንዘብ አጠቃቀም ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የሚቀርብለትን ሪፖርት በማጠቃለል በየስድስት ወሩ፣ እንዲሁም በአንቀጽ 15/2 መሠረት የተመረመረ የፈንዱን ሂሣብ ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በየዓመቱ ሂሳቡ በተመረመረ በአንድ ወር ውስጥ ለገንዘብ ሚኒስቴር እንዳላቀረበ እና በአዋጁ የተሰጠውን ሃላፊነት እንዳልተወጣ ለማወቅ ተችላል፤፤

35. በሌላ መልኩ ባንኩ በቀን 01/10/2009 ዓ/ም በደብዳቤ ቀጥር ማኢ-30/19/12 በውክልና ስልጣኑን ለሰጣቸው ለዘጠኙ ክልሎች እና ለሁለቱ ከተማ መስተዳድሮች የፋይናንስ ቢሮዎች የተመረመረ የፈንዱን ሂሣብ ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በየዓመቱ ሂሳቡ በተመረመረ በአንድ ወር ውስጥ ባንኩን ወክለው ለገንዘብ ሚኒስቴር እየላኩ ስለመሆናቸው የሚከታተልበት የአሰራር ስርአት እንደሌለው በቀን 25/11/10 ዓ/ም የሚመለከታቸው የባንኩ የስራ ኃላፊዎች ከኦዲት ቡድኑ ጋር ባካሄዱት ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

36. ከዚህ በተጨማሪ ባንኩ ውክልና የሰጣቸው በኦዲቱ በናሙና የታዩ የአማራ፣ትግራይ፣ የኦሮሚያና የሀረሪ ክልል የፋይናንስ ቢሮዎች እንዲሁም የአዲስ አበባና የድሬደዋ መስተዳድር የፋይናንስ ቢሮዎች በውክልና በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት ስለፈንዱ ገንዘብ አጠቃቀም በየዓመቱ ሂሳቡ በተመረመረ በአንድ ወር ውስጥ ባንኩን ወክለው ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት የማያቀርቡ መሆኑ ገልፀዋል፤፤ከዚህ በተጨማሪ የብድርና ቁጠባ ተቋም አክሲዮን/ማህበራት የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ከሰጡት መልስ እና ለገንዘብ ሚኒስቴር የገንዘብ ስርጭቱን እና ገንዘብ እንዲላክላቸው ብቻ የጠየቁበትን ከሚያሳዩ የጽሁፍ ሰነዶች በስተቀር ስለፈንዱ ገንዘብ አጠቃቀም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማቱ በየስድስት ወሩ የተጠቃለለ፣ እንዲሁም በአንቀጽ 15/2

መሠረት የተመረመረ የፈንዱን ሂሣብ ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር እንደማይልኩ ለማወቅ ተችሏል፡፡

37.ስለጉዳዩ የባንኩ የበላይ ኃላፊዎች ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ፤ ባንኩ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ከገንዘብ ሚኒስቴር እና ከየክልሉ የፋይናንስ ቢሮዎች ጋር በተፈራረመው ውክልና መሰረት ሰነዱ ላይ ኃላፊነት የተሰጠው ለየክልል የፋይንንስ ቢሮዎች መሆኑ በውክልና ሰነዱ አንቀፅ 4 ተ.ቁ 1-8 መመልከት እንደሚቻል ገልፀዋል፡፡

38.በተጨማሪ ባለድርሻ አካላት ባንኩ ባዘጋጀው የተዘዋዋሪ ፈንድ ማስተዳደሪያ ረቂቅ መመሪያ ያላቸውን ቅሬታ ተከትሎ የገንዘብ ሚኒስቴር ከወቅቱ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚንስቴር እና የተለያዩ ከፍተኛ የመንግስት አካላት ጋር በተደረገ ልዩ ስብሰባ በጉዳዩ ላይ በጥልቀት ከተወያዩ በኋላ ባንኩ በአዋጅ ከተሰጠው ፈንዱን የማስተዳደር ተግባር እንዲያይ በጠቅላይ ሚንስትሩ በተቋቋመ ኮሚቴ ለስራው ቅልጥፍና ሲባል ባንኩ በአዋጅ ከተሰጠው ስልጣን እንዲወጣ የተደረገ መሆኑ የባንኩ የበላይ ኃላፊዎች በኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ገልጸዋል፡፡

39.የባንኩ የበላይ ኃላፊ ይህንን ይበሉ እንጂ፡-

- የኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ ባንኩ የተመረመረ የፈንዱ ሂሳብ ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር ለገንዘብ ሚኒስቴር ስለመላኩና አለመላኩ በማስረጃ በማስደገፍ ምላሽ እንዲሰጥበት የጠየቀ ሲሆን፤ የተሰጠው ምላሽ የሰነዱ ኃላፊነት ለየክልል የፋይንንስ ቢሮዎች የተሰጠ መሆኑ የሚያስረዳ በመሆኑ የተጠየቀው ጥያቄና የተሰጠው ምላሽ የማይገናኝ በመሆኑ፤ እና ባንኩ በአዋጅ የተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት በአዋጅ እስካልተሻረ ድረስ በማንኛውም መልኩ ለሌላ ሦስተኛ ወገን በውክልናም ሆነ በሌላ መልኩ የማስተላለፍ ስልጣን የሌለው በመሆኑ ለነባራዊ ሁኔታው እና በኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ የተሰጠውም ምላሽ በኦዲቱ ተቀባይነት የለውም፡፡

40.በመሆኑም ባንኩ በአዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀጽ 11/2 መሠረት ስለፈንዱ ገንዘብ አጠቃቀም ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የሚቀርብለትን ሪፖርት በማጠቃለል በየስድስት ወሩ፣ እንዲሁም በአንቀጽ 15/2 መሠረት የተመረመረ የፈንዱን ሂሣብ ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በየዓመቱ ሂሳቡ በተመረመረ በአንድ ወር ውስጥ

ለገንዘብ ሚኒስቴር ባለመላኩ እንዲሁም ባንኩ ይህን ሃላፊነቱን በውክልና ሰጥቻቸዋለሁ ያላቸው የክልል የፋይናንስ ቢሮዎች የተሰጣቸውን ሃላፊነት ያልተወጡ በመሆኑ ምክንያት በ2009 እና በ2010 ዓ/ም ከ9 ቢሊዮን ብር በላይ ከመንግስት ወጪ ሆኖ ለተጠቃሚዎች የተሰራጨው ገንዘብ ለታለመለት አላማ ስለመዋሉ ወይም አለመዋሉ እንዳይታወቅ አድርጓል፡፡

41.በተጨማሪም የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የተዘዋዋሪ ፈንዱን የገንዘብ አጠቃቀም የሚመለከት **የተመረመረ** የሂሳብ መግለጫ ሪፖርት በየደረጃው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በወቅቱ ማቅረብ እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

ባንኩ የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች ማስተላለፉን በተመለከተ

42.በየኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም የወጣው አዋጅቁጥር 995/2009 ዓ/ም የባንኩ ተግባርና ኃላፊነት አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የአዋጁ አንቀፅ 9/1 እና 2 እንደሚገልጸው /የክልሉን ወጣቶች ቁጥር/ መሠረት በማድረግ የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች ሊያስተላልፍ ይገባል፡፡

43.ሆኖም ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ከሚመለከታቸው የባንኩ የስራ ሃላፊዎች እና በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው ከታዩ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የስራ ሃላፊዎች ጋር ባካሄዳቸው ቃለ መጠይቆችና የዶክመንት ክለሳዎች መሰረት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አንቀፅ 9/1 እና 2 / መሰረት የክልሉን ወጣቶች ቁጥር/ መሠረት በማድረግ የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች እንዳላስተላለፈና በአዋጅ የተሰጠውን ሃላፊነት እንዳልተወጣ በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችላል፡፡ እንዲሁም ባንኩ ውክልና የሰጣቸው የዘጠኙ ክልሎች እና የሁለቱ ከተማ መስተዳድር ፋይናንስ ቢሮዎች 5 ቢሊዮን የፈንዱ ገንዘብ የክልላቸውን ወጣት ቁጥር መሰረት በማድረግ የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች ያስተላለፉ መሆናቸው ነገር ግን ከ4.1 ቢሊዮን ብር በላይ የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች ሲያስተላልፉ

የክልላቸውን ወጣት ቁጥር መሰረት በማድረግ ስለማስተላለፋቸው የሚያስረዳ ሰነድ በኦዲቱ ወቅት ያልቀረበ መሆኑ ከቀረቡ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

44. ለወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ከተመደበው 10 **ቢሊዮን** ብር ውስጥ **ከ9 ቢሊዮን** ብር በላይ ወጪ ሆኖ ለተጠቃሚዎች የተሰራጨው የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች የሚያስተላልፍበትን በገንዘብ ሚኒስቴር ደንቦችና ሁኔታዎች ሳይዘጋጅና ስራ ላይ ሳይውል በመሆኑ ገንዘቡ በክልልና በከተማ መስተዳድር የፋይናንስ ቢሮዎች ለተጠቃሚዎች የተሰራጨው በአዋጁ መሰረት በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባወጣቸው ደንቦችና ሁኔታዎች ሳይሆን፤ ደንብ የማውጣት በአዋጁ ስልጣን ባልተሰጣቸው በማይክሮ ፋይናንሶች በተዘጋጁ እና ወጥነት በሌላቸው ደንቦች መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለትግራይ፣ አማራ፣ ኦሮሚያና ሀረሪ ክልሎች እንዲሁም ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ቢሮች፣ ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት እና ለገንዘብ ሚኒስቴር የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ከቀረበው ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

45. ስለጉዳዩ የባንኩ ኃላፊዎች ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ፤ ባንኩ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ በተመለከተ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ገንዘብ ሚኒስቴር ባለበት በውክልና ለክልሎች እና ለከተማ መስተዳድር ፋይናንስ ቢሮዎች የሰጠ በመሆኑ፤ ስራው መሰራት ያለበት በነሱ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

46. በተጨማሪ ባለድርሻ አካላት ባንኩ ባዘጋጀው የተዘዋዋሪ ፈንድ ማስተዳደሪያ ረቂቅ መመሪያ ያላቸውን ቅሬታ ተከትሎ የገንዘብ ሚኒስቴር ከወቅቱ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚንስቴር እና የተለያዩ ከፍተኛ የመንግስት አካላት ጋር በተደረገ ልዩ ስብሰባ በጉዳዩ ላይ በጥልቀት ከተወያዩ በኋላ ባንኩ በአዋጅ ከተሰጠው ፈንዱን የማስተዳደር ተግባር እንዲያይ በጠቅላይ ሚንስትሩ በተቋቋመ ኮሚቴ ለስራው ቅልጥፍና ሲባል ባንኩ በአዋጅ ከተሰጠው ስልጣን እንዲወጣ የተደረገ መሆኑ የባንኩ የበላይ ኃላፊዎች በኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ገልጸዋል፡፡

47. የባንኩ የበላይ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ ፤ ባንኩ በአዋጅ የተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት በአዋጅ እስካልተሻረ ድረስ በማንኛውም መልኩ ለሌላ ሦስተኛ ወገን በውክልናም ሆነ በሌላ መልኩ የማስተላለፍ ስልጣን የሌለው በመሆኑ ለነባራዊ

ሁኔታው እና በኦዲቱ መውጫ ስብሰባ የተሰጠው ምላሽ በኦዲቱ ተቀባይነት የለውም፡፡

48.በመሆኑም ባንኩ በአዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀፅ 9/1 እና 2 በተሰጠው ስልጣን መሰረት በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች እንዲተላለፍ ባለማድረጉ ይህ ስራ በውክልና በክልል የፋይናንስ ቢሮዎች በኩል ወጥ የሆነ ድንብና መመሪያ ባልተዘጋጀበት እና ግልፅ የአሰራር ስርአት ባልተዘጋጀበት ሁኔታ ለተጠቃሚዎች በመሰራጨቱ በፈንዱ ተጠቃሚ በሆኑ ወጣቶች በፕሮጀክት ግምገማ፤በብድር ማፅደቅ እና በብድር አመላለስ ወቅት በርካታ ቅሬታዎች እና የአሰራር ችግሮች እንዲከሰቱ አድርጓል፡፡

49.በአጠቃላይ ባንኩ የክልሉን ወጣቶች ቁጥር/ መሠረት በማድረግ የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች በራሱ ሊያከናወነው ባለመቻሉ ስልጣን የሌላቸው የክልል ፋይናንስ ቢሮዎች ይህንን ተግባር ሲያከናውኑ ህጋዊ ያልሆኑ አካሄዶችና ተግባራት ቢፈጠሩ ተጠያቂ ለማድረግ የሚደረገው የህግ አግባብ ወይም ጥረት ውጤታማ እንዳይሆን ያለው እድል ሰፊ እንዲሆን ከማድረጉም ባሻገር የወጣቶች ተጠቃሚነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ይፈጥራል ፡፡

ባንኩ የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በሌሉባቸው አካባቢዎች ቅርንጫፍ ባንኮች ተክተው እንዲሰሩ ማድረጉን በተመለከተ

50. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የአዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀጽ 11/1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በአዋጁ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በሌሉባቸው አካባቢዎች ቅርንጫፍ ባንኮች የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማትን ተክተው እንዲሰሩ ሊያደርግ ይገባል፡፡

51.ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከባንኩ የስራ ሃላፊዎች እና በናሙና ተመርጠው ከታዩት የክልል የፋይናንስ ቢሮ የስራ ሃላፊዎች ጋር ባካሄዳቸው ቃለመጠይቆች እና የዶክመንት ክለሳዎች መሰረት ባንኩ የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በሌሉባቸው አካባቢዎች ቅርንጫፍ ባንኮች የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማትን ተክተው እንዲሰሩ እንዳላደረገ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

52.እንዲሁም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአዋጁ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለዘጠኙ ክልሎች እና ለሁለቱ ከተማ መስተዳድር የፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች

በውክልና ሲሰጥ በውክልና ውሉ ላይ እንዲካተት እንዳልተደረገ እና አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በሌሉባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ የኢትዮጵያ ወጣቶች የፈንዱ ተጠቃሚ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ባንኩ የሚያውቅበት ሁኔታ እንደሌለ በቀን 25/11/2010 ዓ/ም ከሚመለከታቸው የባንኩ የስራ ኃላፊዎች ጋር የኦዲት ቡድኑ ባካሄደው ቃለመጠይቅ ገልጸዋል፡፡

53.በተጨማሪም የክልልና የከተማ መስተዳድር የፋይናንስ ቢሮዎች የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በሌሉባቸው አካባቢዎች ቅርንጫፍ ባንኮች የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማትን ተክተው እየሰሩ ስለመሆናቸው እና አለመሆናቸው መረጃ እንደሌላቸው በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ገልጸዋል፡፡

54.ስለጉዳዩ የባንኩ ኃላፊዎች ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ፤ ባንኩ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ በተመለከተ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት የገንዘብ ሚኒስቴር ባለበት በውክልና ለክልሎች እና ለከተማ መስተዳድር ፋይናንስ ቢሮዎች የሰጠ በመሆኑ፤ ስራው መሰራት ያለበት በነሱ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

55.በተጨማሪ ባለድርሻ አካላት ባንኩ ባዘጋጀው የተዘዋዋሪ ፈንድ ማስተዳደሪያ ረቂቅ መመሪያ ያላቸውን ቅሬታ ተከትሎ የገንዘብ ሚኒስቴር ከወቅቱ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚንስቴር እና የተለያዩ ከፍተኛ የመንግስት አካላት ጋር በተደረገ ልዩ ስብሰባ በጉዳዩ ላይ በጥልቀት ከተወያዩ በኋላ ባንኩ በአዋጅ ከተሰጠው ፈንዱን የማስተዳደር ተግባር እንዲያይ በጠቅላይ ሚንስትሩ በተቋቋመ ኮሚቴ ለስራው ቅልጥፍና ሲባል ባንኩ በአዋጅ ከተሰጠው ስልጣን እንዲወጣ የተደረገ መሆኑ የባንኩ የበላይ ኃላፊዎች በኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ገልጸዋል፡፡

56.የባንኩ የበላይ ኃላፊ ይህንን ይበሉ እንጂ ፤ በአዋጅ የተሰጠ ስልጣንና ኃላፊነት ማንሳት ወይም ለሌላ አካል ማስተላለፍ የሚቻለው በአዋጅ ብቻ በመሆኑ፤ እንዲሁም ባንኩ በአዋጅ ከተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት አንዱ የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በሌሉባቸው አካባቢዎች ቅርንጫፍ ባንኮች የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማትን ተክተው እንዲሰሩ ሊያደርግ እንደሚገባ የተገለፀ በመሆኑ እና ይህንን ጉዳይ የሚመለከተውን ሃላፊነቱን በተመለከተ በውክልና ሰነዱ ላይ እንዳልተገለጸና ለክልል የፋይናንስ ቢሮዎችም ውክልና ያልተሰጠ በመሆኑ በባንኩ የስራ ሃላፊወች ለነባራዊ

ሁኔታው እና በኦዲቱ መውጫ ስብሰባ የተሰጠው መልስ በኦዲቱ ተቀባይነት የለውም፡፡

57.ባንኩ የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በሌሉባቸው አካባቢዎች ቅርንጫፍ ባንኮች የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማትን ተክተው እንዲሰሩ ባለማድረጉ የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በሌሉባቸው የአገሪቱ የተለያዩ ወረዳዎች እና ቀበሌዎች የሚገኙ ወጣቶች ከተዘዋዋሪ ፈንዱ እኩል ተጠቃሚ እንዳይሆኑ አድርጓል፡፡

ባንኩ የፈንዱን ሂሳብ እንዲመረመር ማድረጉን በተመለከተ

58.ባንኩ በአዋጅ ቁጥር 995/2009 በአንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 2 / መሰረት የፈንዱን ሂሣብ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ እንዲመረመር ሊያደርግ ይገባል፡፡

59.ይሁን እንጂ ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ከባንኩ የስራ ሃላፊዎች እና ከክልል የፋይናንስ ቢሮ የስራ ሃላፊዎች ጋር ባካሄደቸው ቃለመጠይቆች እና የዶክመንት ክለሳዎች መሰረት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የፈንዱን ሂሣብ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ እንዲመረመር እንዳላደረገ እና በአዋጅ የተሰጠውን ሃላፊነት እንዳልተወጣ ታውቋል፤፤

60.እንዲሁም ባንኩ አዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ.ም ከሚፈቅደው ውጭ ፈንዱን አስመልክቶ ውክልና የሰጣቸው የክልል ፋይናንስ ቢሮዎችም የፈንዱን ሂሣብ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ እንዲመረመር እንዳላደረጉ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ በናሙና ተመርጠው ከታዩ የክልል የፋይናንስ ቢሮ የስራ ሃላፊዎች ጋር ባካሄደው ቃለ መጠይቅ አረጋግጧል፡፡

61.ስለጉዳዩ የባንኩ ኃላፊዎች ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ፤ ባንኩ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ በተመለከተ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ገንዘብ ሚኒስቴር ባለበት በውክልና ለክልሎች እና ለከተማ መስተዳድር ፋይናንስ ቢሮዎች የሰጠ በመሆኑ፤ ስራው መሰራት ያለበት በነሱ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

62.በተጨማሪ ባለድርሻ አካላት ባንኩ ባዘጋጀው የተዘዋዋሪ ፈንድ ማስተዳደሪያ ረቂቅ መመሪያ ያላቸውን ቅሬታ ተከትሎ የገንዘብ ሚኒስቴር ከወቅቱ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚንስቴር እና የተለያዩ ከፍተኛ የመንግስት አካላት ጋር በተደረገ ልዩ ስብሰባ በጉዳዩ ላይ በጥልቀት ከተወያዩ በኋላ ባንኩ በአዋጅ ከተሰጠው ፈንዱን

የማስተዳደር ተግባር እንዲያይ በጠቅላይ ሚንስትሩ በተቋቋመ ኮሚቴ ለስራው ቅልጥፍና ሲባል ባንኩ በአዋጅ ከተሰጠው ስልጣን እንዲወጣ የተደረገ መሆኑ የባንኩ የበላይ ኃላፊዎች በኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ገልጸዋል፡፡

63.የባንኩ የበላይ ኃላፊ ይህንን ይበሉ እንጂ ፤ ባንኩ በአዋጅ የተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት በአዋጅ እስካልተሻረ ድረስ በማንኛውም መልኩ ለሌላ ሦስተኛ ወገን በውክልናም ሆነ በሌላ መልኩ የማስተላለፍ ስልጣን የሌለው በመሆኑ ለነባራዊ ሁኔታው እና በኦዲት መውጫ ስብሰባ የተሰጠውም ምላሽ በኦዲቱ ተቀባይነት የለውም፡፡

64.ባንኩ ፈንዱን አስመልክቶ ከላይ ባዋጁ በዝርዝር የተሰጡትን ሃላፊነቶች ያልተወጣ እና የፈንዱንም ሂሳብ በአዋጅ መሰረት በየአመቱ ኦዲት ያላስደረገ በመሆኑ እንዲሁም አዋጁ ከሚፈቅደው ውጭ ባንኩ ውክልና የሰጣቸው የክልል የፋይናንስ ቢሮዎችም በተሰጣቸው ውክልና መሰረት ያልሰሩ በመሆኑና የፈንዱም ሒሳብ በህጉ በተገለፀው መሰረት በየአመቱ ኦዲት ባለመደረጉ የፈንዱ ሂሳብ ስራ ላይ እየዋለበት ያለው አካሄድ ውጤታማ ላይሆን እንደሚችል የሚያሳዩ ችግሮች መኖራቸውን የኦዲት ቡድኑ ባካሄዳቸው የዶክመንት ክለሳዎችና የመስክ ጉብኝቶች የሚከተሉትን ችግሮች ለማሳያነት ቀርበዋል፤-

65.ባንኩ አዋጁ ከሚፈቅደው ውጪ የወከላቸው በሁሉም ክልል የሚገኙ የፋይናንስ ቢሮዎች በአካባቢያቸው በሚገኙ ማይሮፋይናንስ ተቋማት በኩል ከ9.1 ቢሊየን ብር በላይ ለተጠቃሚዎች በብድር መልክ እንዲሰራጭ ሲያደርጉ በአዋጁ መሰረት የገንዘብ ሚኒስቴር ባንኩ በማይክሮ ፋይናንስ በኩል የፈንዱን ገንዘብ ለተጠቃሚዎች የሚያስተላልፍበት ደንቦችና ሁኔታዎች ማዘጋጀቱንና ስራ ላይ እንዲውል ማድረጉን ሳያረጋግጡና ሳይጠይቁ በመሆኑ፤

66.በ10/04/2011 ዓ/ም ከድሬ ብድርና ቁጠባ ተቋም በተገኘ የሰነድ ማስረጃ መሰረት፡-

- በድሬደዋ ከተማ ከሚገኙ ዘጠኝ ቀበሌዎች በድምሩ ብር 8,695,015 ከፈንዱ ብድር የወሰዱ 105 ኢንተርፕራይዞች በስራ ላይ የማይገኙ/የሌሉ መሆናቸው በ10/04/2011 ዓ/ም ከድሬ ብድርና ቁጠባ ተቋም በተገኘ የሰነድ ማስረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

- እንዲሁም በድሬደዋ መስተዳድር በገጠር ከሚገኙ ሦስት ክላስተሮች በድምሩ ብር 1,395,000 ከፈንዱ ብደር የወሰዱ 19 ኢንትርፕራይዞች በስራ ላይ የማይገኙ/የሌሉ መሆናቸው በ10/04/2011 ዓ/ም ከድሬ ብድርና ቁጠባ ተቋም በተገኘ የሰነድ ማስረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

67.የድሬደዋ አስተዳደር በከተማ ቀበሌዎች የወጣት ተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ የብድር አጠቃቀም ሪፖርት በተመለከተ ሰኔ 2010 ከድሬ ብድርና ቁጠባ ተቋምና ከድሬደዋ ወጣቶችና ስፖርት ኮሚሽን በተገኘ ሰነድ መሰረት ብድር ወስደው ወደ ስራ የገቡ ኢንትርፕራይዞች የብድር አመላለስ ላይ ስጋት መኖሩን ገልፀዋል፡፡

68.በጥር 08/2011 ዓ/ም ከአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማህበር ከም/ማ/ዳይሬክተር ኦፕሬሽን ዘርፍ በተገኘ የሰነድ ማስረጃ መሰረት፡-

- በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ከአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም ከተዘዋዋሪ ፈንድ ብር 21,045,000.00 ብድር የወሰዱ 124 ኢንትርፕራይዞች በአሁኑ ወቅት በስራ ላይ የሌሉ መሆናቸው ከተቋሙ በተገኘ የጽሑፍ ማስረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

69.በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር የተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ ተጠቃሚ የሆኑ ኢንትርፕራይዞች ላይ በተደረገ የመስክ ምልከታ በተገኘው መረጃ መሰረት፡-

- ✓ በየካ ክ/ከተማ በወረዳ 10 እየሰሩ የሚገኙ አዲስአለም ወሰኔና ጓደኞቹ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች ምርት ስራ ኢንትርፕራይዝ ተደራጅተው ብድር የወሰዱ የወጣቶች ብዛት 5 ሲሆን አሁን በስራው ላይ የሚገኝ ግን አንድ ብቻ መሆኑና አራቱ ስራ ላይ የሌሉ መሆናቸው፡፡
- ✓ በአራዳ ክ/ከተማ በወረዳ 01 የሚገኝ ሊዲያ ይኩኖና ጓደኞቻቸው የምግብ ዝግጅት ስራ ኢንትርፕራይዝ ተደራጅተው ብድር የወሰዱ የወጣቶች ብዛት 30 ሲሆን አሁን በስራው ላይ የሚገኙ አባላት ብዛት 22 ብቻ መሆናቸው፡፡

70.በመሆኑም ባንኩ በአዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ.ም በአንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 2 / መሰረት የፈንዱን ሂሣብ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ እንዲመረመር ባለማድረጉ እንዲሁም አዋጁ ከሚፈቅደው ውጭ ውክልና የተሰጣቸው የክልል ፋይናንስ ቢሮዎችም የፈንዱን ሂሣብ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ እንዲመረመር አለማድረጋቸው ለፈንዱ

የተመደበው 10 ቢሊዮን ብር ፈንዱ ለታቀደለት አላማ የመንግስትን የፋይናንስ ህግና መመሪያን ተከትለው ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ስራ ላይ ስለመዋሉ ለማረጋገጥ የማያስችል ሲሆን አሰራሩ ይህን ከፍተኛ የሆነ የመንግስት ገንዘብ ለብልሹ አሰራር፣ ለምዝበራና ለብክነት እንዲጋለጥና የተሰጠውም ብድር በወቅቱ እንዳይሰበሰብ ያደርጋል፡፡

ክፍል ሦስት

የኦዲቱ መደምደሚያ (Audit Conclusion)

72.የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በየኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ማቋቋያ አዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ/ም አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ሂሣብን በሚመለከት የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ያልያዘ እና በአዋጅ የተሰጠውን ሃላፊነት ያልተወጣ መሆኑ፡፡ እንዲሁም አዋጁ ከሚፈቅደው ውጭ ባንኩ በአዋጁ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት በቀን 01/10/2009 ዓ/ም በደብዳቤ ቀጥር ማኢ-30/19/12 ለዘጠኙ ክልሎች እና ለሁለቱ ከተማ መስተዳድር የፋ/ኢ/ል/ ቢሮዎች በውክልና ሲሰጥ በውክልና ውሉ ላይ የሂሳብ መዛግብት መያዝ እንዳለባቸው እንዲካተት ያላደረገ መሆኑ እና የክልል የፋይናንስ ቢሮዎችም ፈንዱን በሚመለከት የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብትን ያልያዙ መሆኑ፡፡

73.ባንኩ በአዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀጽ 11/2 መሠረት ስለፈንዱ ገንዘብ አጠቃቀም ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የሚቀርብለትን ሪፖርት በማጠቃለል በየስድስት ወሩ፣ እንዲሁም በአንቀጽ 15/2 መሠረት የተመረመረ የፈንዱን ሂሣብ ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በየዓመቱ ሂሳቡ በተመረመረ በአንድ ወር ውስጥ ለገንዘብ ሚኒስቴር አላቀረበም፡፡ እንዲሁም አዋጁ ከሚፈቅደው ውጭ ባንኩ በአዋጁ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት በቀን 01/10/2009 ዓ/ም በደብዳቤ ቀጥር ማኢ-30/19/12 ውክልና የሰጣቸው ዘጠኙ ክልሎች እና ሁለቱ ከተማ መስተዳድር የፋ/ኢ/ል/ ቢሮዎች ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የሚቀርብላቸውን ሪፖርት በማጠቃለል በየስድስት ወሩ፣ እንዲሁም የተመረመረ የፈንዱን ሂሣብ ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በየዓመቱ ሂሳቡ በተመረመረ በአንድ ወር ውስጥ ለገንዘብ ሚኒስቴር ያልላኩ መሆናቸው፡፡

74.የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀፅ 9/1 እና 2 /የክልሉን ወጣቶች ቁጥር/ መሠረት በ2009 እና 2010 በጀት አመት የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች እንዲተላለፍ አላደረገም፡፡

እንዲሁም ከአዋጅ ውጭ በሆነ መልኩ ውክልና የሰጣቸው የዘጠኙ ክልሎች እና የሁለቱ ከተማ መስተዳድር ፋይናንስ ቢሮዎች፣ ገንዘብ ሚኒስቴር ባንኩ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ገንዘቡ ወደ ተጠቃሚዎች የሚያስተላልፉበት ደንብና ሁኔታዎች ባለወጣበት እና በአዋጁ ስልጣን ባልተሰጣቸው በየክልሉ የሚገኙ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ባዘጋጁቸው ወጥነት በሌላቸው ደንቦች እና ሁታዎች ከ9.1 ቢሊዮን ብር በላይ ለተጠቃሚዎች እንዲተላለፍ መደረጉ፡፡

75. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የአዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀጽ 11/1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በሌሉባቸው አካባቢዎች ቅርንጫፍ ባንኮች የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማትን ተክተው እንዲሰሩ አላደረገም፡፡ እንዲሁም አዋጁ ከሚፈቅደው ውጭ ባንኩ በአዋጁ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት በቀን 01/10/2009 ዓ/ም በደብዳቤ ቀጥር ማኢ-30/19/12 ለዘጠኙ ክልሎች እና ለሁለቱ ከተማ መስተዳድር የፋ/ኢ/ል/ ቢሮዎች በውክልና ሲሰጥ በውክልና ውሉ ላይ የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በሌሉባቸው አካባቢዎች ቅርንጫፍ ባንኮች የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማትን ተክተው መስራት እናዳለባቸው እንዲካተት ያላደረገ መሆኑ እና አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በሌሉባቸው በኢትዮጵያ ገጠር ወረዳዎች የሚኖሩ ወጣቶች የፈንዱ ተጠቃሚ መሆናቸውና አለመሆናቸው የማይታወቅ መሆኑ፡፡

76. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የ2009 ዓ/ም እና የ2010 ዓ/ም የፈንዱን ሂሣብ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ እንዲመረመር አላደረገም፤ እንዲሁም ባንኩ በአዋጅ ከተሰጠው ስልጣን ውጭ ውክልና የሰጣቸው ሁሉም በናሙና የታዩት የትግራይ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ የሀረሪ ክልሎች፤ የአዲስ አበባ እና የድሪደዋ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ቢሮዎች የፈንዱን ሂሳብ በዋናው ኦዲተር ወይም እነሱ በሰየሙት ኦዲተር በየዓመቱ እንዲመረመር ያላደረጉ መሆናቸው፡፡

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማስተዳደር በአዋጅ 995/2009 ዓ/ም በክፍል ሁለት አንቀጽ ሰባት ኃላፊነት ቢሰጠውም፤ ባንኩ የመወከል እና በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣን አሳልፎ ለሌሎች አካላት የመስጠት

ስልጣን ሳይኖረው ስራውን ሳይጀምረው ለዘጠኙ ክልሎች እና ለሁለቱ ከተማ መስተዳድር የፋይናንስ ቢሮዎች በውክልና ስልጣኑን የሰጣቸው መሆኑ፡፡

ክፍል አራት

የኦዲቱ ማሻሻያ ሀሳብ (Recommendation)

78.ባንኩ ለወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ የተመደበው 10 ቢሊዮን ብር ለማስተዳደር በአዋጅ ቁጥር 995/2009 የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ህጋዊ በሆነ መልኩ በአዋጅ እስካልተሻረ ድረስ የፈንዱን ሂሣብ በሚመለከት የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት እንዲይዝ ቢደረግ በአፈጻጸም ወቅት በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የተፈጠሩ ማጭበርበር እና ሙስና ካለ በመለየት የመንግስትና የህዝብ ገንዘብ ተመላሽ ከማድረግም በላይ ድርጊቱን የፈጸሙ አካላት ተጠያቂ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚደረገው ሂደት የተሳካ እንዲሆን ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡እንዲሁም ለፈንዱ ከተመደበው ገንዘብ ከ9 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ሆኖ እስኪሰራጭ የፈንዱን ሂሣብ በሚመለከት የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት እንዲያዝ ያላደረጉ የሚመለከታቸው አካላት በመለየት ተጠያቂ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይገባል፡፡

79.ባንኩ በአዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀጽ 11/2 መሠረት ስለፈንዱ ገንዘብ አጠቃቀም ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የሚቀርብለትን ሪፖርት በማጠቃለል በየስድስት ወሩ፣ እንዲሁም በአንቀጽ 15/2 መሠረት የተመረመረ የፈንዱን ሂሣብ ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በየዓመቱ ሂሳቡ በተመረመረ በአንድ ወር ውስጥ ለገንዘብ ሚኒስቴር እንዲላክ ቢያደርግ ለፈንዱ የተመደበውን 10 ቢሊዮን የመንግስት ገንዘብ በምን ደረጃ እንደሚገኝ፣ የጠፋ፣ የተጭበረበረና ከታለመለት አላማ ውጪ የዋለ ገንዘብ ካለ በወቅቱ ክትትልና ቁጥጥር በማደረግ ተመላሽ እንዲሆንና ይህንን ተግባር የፈጸሙ አካላትም በህግ ተጠያቂ እንዲሆኑ የሚደረገውን ሂደት የተሳካ እንደሆን ይረዳል፡፡ በተጨማሪ ባንኩ የ2009 ዓ/ም እና የ2010 ዓ/ም ስለፈንዱ ገንዘብ አጠቃቀም ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ሪፖርት እንዲቀርብ በማድረግ፤ የቀረበውን በማጠቃለል በየስድስት ወሩ፣ እንዲሁም በአንቀጽ 15/2 መሠረት የተመረመረ የፈንዱን ሂሣብ ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በየዓመቱ ሂሳቡ

በተመረመረ በአንድ ወር ውስጥ ለገንዘብና ሚኒስቴር እንዲላክ ባላደረጉ የሚመለከታቸው አካላት ህጋዊ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

80. ባንኩ ለወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ የተመደበው 10 ቢሊዮን ብር ለማስተዳደር በአዋጅ ቁጥር 995/2009 የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ህጋዊ በሆነ መልኩ በአዋጅ እስካልተሻረ ድረስ በአዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀፅ 9/1 እና 2 /የክልሉን ወጣቶች ቁጥር/ መሠረት የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይንንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች እንዲተላለፍ ሊያደርግ ወይም መተላለፉን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

81. እንዲሁም ህጋዊ ባልሆነ መልኩ ውክልና የሰጣቸው ዘጠኙ ክልሎች እና የሁለቱ ከተማ መስተዳድር ፋይናንስ ቢሮዎች ገንዘብ ሚኒስቴር ባንኩ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ገንዘቡ ወደ ተጠቃሚዎች የሚያስተላልፉበት ደንብና ሁኔታዎች ባላወጣበት እና ህጋዊ ባልሆኑ ደንቦች ከ9 ቢሊዮን ብር በላይ ለተጠቃሚዎች እንዲተላለፍ ሲደረግ ክትትል እና ቁጥጥር ባላደረጉ የሚመለከታቸው የባንኩ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች በህግ ተጠያቂ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይገባል፡፡

82. በአዋጅ የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት በህጋዊ አዋጅ እስካልተሻረ ድረስ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የአዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀጽ 11/1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በሌሉባቸው አካባቢዎች ቅርንጫፍ ባንኮች የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማትን ተክተው እንዲሰሩ በማድረግ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በሌሉባቸው በኢትዮጵያ ገጠር ወረዳዎች የሚኖሩ ወጣቶች ከተዘዋዋሪ ፈንዱ እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይገባል፡፡ እንዲሁም በ2009 እና 2010 በጀት አመት ይህንን ተግባር በአግባቡ ባልተወጡ የሚመለከታቸው የባንኩ አካላት ህጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

83. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያለፈው የ2009 ዓ/ም እና የ2010 ዓ/ም እና የቀጣይ አመታትም የፈንዱን ሂሣብ በዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ እንዲመረመር ሊያደርግ ይገባል፤ እንዲሁም ያለፈው የ2009 እና የ2010 በጀት አመት የፈንዱን ሂሣብ ማስመርመር ሲገባቸው ተግባራቸውን ያልተወጡ የሚመለከታቸውን የባንኩ አካላት በመለየት ተጠያቂ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይገባል፡፡

በኦዲቱ ወቅት ለተደረገልን ትብብር እናመሰግናለን!

አባሪዎች

አባሪ 1-የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ድርጅታዊ መዋቅር /C Level/



አባሪ 2- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የመመዘኛ መስፈርት

የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶቹን ለማዘጋጀት መሰረት ከሆኑት ዋና ዋናዎቹ የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጅ 995/2009 እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በቀን 01/10/2009 ዓ/ም በደብዳቤ ቀጥር ማኢ.-30/19/12 በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት በውክልና ለዘጠኙ ክልሎች እና ለሁለቱ ከተማ መስተዳድሮች የፋይናንስ ቢሮዎች የሰጠበት ሰነድ ናቸው፡፡

የመመዘኛ መስፈርት Evaluative Criteria
1. ባንኩ የፈንዱን ሂሣብ በሚመለከት የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ሊይዝ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- /የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ/ም የባንኩ ተግባርና ኃላፊነት አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 1 /**
2. ባንኩ በአዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀጽ 11/2 መሠረት ስለፈንዱ ገንዘብ አጠቃቀም ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የሚቀርብለትን ሪፖርት በማጠቃለል በየስድስት ወሩ፣ እንዲሁም በአንቀጽ 15/2 መሠረት የተመረመረ የፈንዱን ሂሣብ ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በየዓመቱ ሂሳቡ በተመረመረ በአንድ ወር ውስጥ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሊያቀርብ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-/የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ/ም የባንኩ ተግባርና ኃላፊነት አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 3 /**
3. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀፅ 9/1 እና 2 /የክልሉን ወጣቶች ቁጥር/ መሠረት በማድረግ የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይንንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች ሊያስተላልፍ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- /የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ/ም የባንኩ ተግባርና ኃላፊነት አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 1/**

4. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የአዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀጽ 11/1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በሌሉባቸው አካባቢዎች ቅርንጫፍ ባንኮች የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማትን ተክተው እንዲሰሩ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- /የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ/ም የባንኩ ተግባርና ኃላፊነት አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 /**
5. ባንኩ የፈንዱን ሂሣብ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ እንዲመረመር ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-/የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ/ም የባንኩ ተግባርና ኃላፊነት አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 2 /**